# የኢትዮጵያ ሰንደቅ-ዓላማ



*<u>የጥንት ታሪካዊ አመጣጡና የኅብረ-ቀለማቱ ትርጉም</u>*

በልጅነት ድምፅ፤ "ሰንደቅ ዓላማችን!" ስንላት በዜማ፣
አቤት ያላት ውበት፣ ግሩም ያላት ግርማ፣
እንደ እማያት'ማ ሓር፣ ጨርቅ፣ ናት፣
ንገረኝ ያገር ልጅ፣ ምስጢር እንዳላት..."

እያልን፣ ተማሪዎች ሆነን ስናሞግስና ስናዜም ትዝ ይለኛል። "ሰንደቅ-ዓላማ ከቀስተ-ዳመና ወስዶ እግዚአብሔር የሰጠን ባንዴራ ነው!" የሚል የልጆች ወሬም ነበር፤ ኋላም በታሪክና ምሳሌ መጽሓፍ የሰንደቅ-ዓላማ ትርጉም ባጭሩ ተገልጾ፤ "አረንጓዴው ልምላሜና ሃብት፣ ብጫው አበባ፣ ኃይማኖትና ተስፋ፣ ቀዩም ፍሬ፣ ቆራጥነትና፣ መስዋእትነት..." የሚል ስንማር፤ አንዱ ተንኰለኛ ልጅ የግብረ-ገብ አስተማሪውን፣ "የኔታ፣ ምን ዓይነት ተክል ነው ታድያ ፍሬው ከታች፣ አበባው ከላይ፣ ቅጠሉ ከሁሉ በላይ የሆነ?" ብሎ ቢጠይቅ፣ የኔታ፣ "እርኩስ!" ብለው፣ ጆሮውን በጥፊ! ሌላም ልጅ ተቀብሎ፤ "የኔታ፣ አረ ይህስ ድንች ይሆን?" ቢል፣ እርሱም ጥፊውን ልሶ፣ የቀልድ ስሙ "ድንች" ወጣለት። የሰንደቅ-ዓላማ ጥንታዊ ታሪኩና ኣመጣጡ ግን ፈጽሞ ሳይነገረን፣ ሳይዘረዘርልን ቀረ።

በየዘመናቱም በአገራችን መሪ ሄዶ መሪ ሲተካ፣ በሰንደቅ ዓላማው የተለያዩ አርማዎችን ሲቀርጹበት ታይቷል። እንግዲያውስ የኢትዮጵያ ሰንደቅ-ዓላማ ታሪካዊ ኣመጣጡና የኅብረ-ቀለማቱ ትርጉም ከኣፈ-ታሪክ ያገኘነውና ከአበው የተማርነውን ከዚህ ቀጥለን ለመግለጽ እንሞክራለን።

በዓለም ጦርነት ሲጀመር ከኣንድ ለኣንድ ትግልና፣ ፍልምያ ታልፎ የአንድ መንደር ጐረምሶች ተባብረው ወደሌላው መንደር ሲጓዙና ሲዘምቱ፣ የሌላው መንደር ጐረምሶችም መክተው ሲዋጓቸው መሆኑ ጥርጥር የለውም። የኣንድ መንደር ጐረምሶች ወደሌላው የሚዘምቱትም ሚስት ለመጥለፍ፣ ከብት ወይም ሌላ ሃብትና ንብረት ለመዝረፍ፣ ወይም ቂም ለመበቀል... ወዘተ መሆኑ ጥያቄ የለውም። በዚህም ጊዜ ከጐረምሶቹ ጠንከር፣ ደፈር፣ ወይም ጠና ያለው፣ ብትር ወይም ጦር መሳይ ይዞ፣ ጠላቶቻቸው ያሉበትን ጉራ በብትሩ እየጠቆመ እንዲያጠቁ ያሳያቸዋል፣ ይመራቸዋል። ይኸም "ረኸርም" ብትር ለመጀመሪያው "ሰንደቅ" ለሚለው ቃል ምንጭ ሆኖ፣ ትርጉሙም ረኸርም የሸምበቆ፣ የቅርቀሃ፣ ወይም የሌላ ዕንጨት ዘንግና ብትር ማለት ነው።

ከጊዜ ብዛት የጦር መሪው ኣለቃና ንጉሥ ይሆንና፣ ጦርነት ሲሄዱ የሚጠቀምባት ብትርም የስልጣን ምልክት ትሆናለች። በጥንታውያን የግብጽ ስእሎችና ምስሎች ነገሥታቱ በትረ-መንግሥት እንደ ጨበጡ ይታያሉ። በመጽሐፍ ቅዱስም ሙሴ በብትሩ ብዙ ተአምራቶችን እንደ ሠራ፣ የእስራኤል ልጆች ጦርነት ሲገጥሙም ብትሩን ሽቅብ ያነሳ እንደ ነበር(1) ተጽፎኣል። በትረ-አሮንም በታቦት ፊት በአንዲት ሌሊት ቅጠል አብቅላ፣ አባበ እንዳበበች፣ ፍሬም እንዳፈራች እናነብባለን።(2)

እየቆየ ሲመጣም የተዋጊዎቹ ቁጥር እየጨመረ ሂዶ፣ ብትሩ ከሩቅ የማይታይ ሲሆን ጊዜ ለማየት የሚመች የቅጠል ዝንጣፍ መያዝ መጣ። ቅጠልም የመሪ ምልክት ሆነ። ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም በአህያ ግልገል ተቀምጦ ሲገባ ሕዝቡ ዘንባባና ሌላ ቅጠል እየዘነጠፈ በመያዝ፣ "ሆሳእና! በጌታ ስም የሚመጣ የዳዊት ልጅ ብሩክ ነው!"(3) እያለ፣ በክብር እንደ ተቀበለው እናነብባለን። የዘንባባ ዝንጣፊና ሌላ ቅጠልም የመሪ ምልክት መሆኑና የዘመኑንም ገዢዎችና መሪዎችንም እንዳስቆጣቸው ተጽፏል።

በሰሜን ኢትዮጵያም መሪን "ባለ ቅጠል" (በዓል ቆጽሊ) ብለው ይጠሩ እንደነበር በጽሑፎችና ኣፈ-ታሪኮች ይገኛል(4)። እንግዲያውስ ቅጠል እንደ ልብ ስለሚገኝ ከማንኛውም ዛፍ ቆርጦ፣ እንደ "ሰንደቅ-ዓላማ" በመያዝ ለጦርነት መምሪያ ስለሚያመች፣ በመጀመሪያው የጦር ዘመቻ በሰንደቅ-ዓላማ ቦታ ሆኖ ኣገልግሏል ቢባል ሓሰት ኣይሆንም። ቅጠላ-ቅጠልም የሃገር ልምላሜና የሃብት ምልክት መሆኑ ኣይደንቅም።

ከነዚህ ሁሉ ጥንታውያን ማስረጃዎችም በነገሥታት ዘመን ሰንደቅ ዓላማ ለመኖሩ፤ ዳዊት በመዝሙሩ፤ "በአምላካችንም ስም ሰንደቅ ዓላማ እናነሳለን" ይላል(5)። ከመንደርና ከቀበሌ ጎረምሶች ጠብ ታልፎ በሃገር ደረጃ ሲደረስ የኢትዮጵያ የመጀመሪያው ባንዴራ ባለ አረንጓዴ ቀለም እንደነበረ እናገኛለን። አረንጓዴ የሚለው ቃልም በትግርኛ "ቅጠልያ" ማለት ሲሆን፣ የቅጠል ቀለም ማለት ነው። ይህም ኅብረ-ቀለም በአክሱም ዘመነ መንግሥት፣ ከክርስቶ ልደት ኣንድ ሺሕ ዓመት በፊት የኢትዮጵያ የነገሥታት ምልክት ሆኖ የቆየ ሲሆን፤ ቅጠል ቀጥቅጠው፣ በጭማቂው የሸማ ጨርቅ ነክረው ይሠሩት እንደነበር ይታወቃል። ይኸ ከሃገራችን ሽማግሎችና ከሊቃውንት አፍ፣ በተለይም ከቅድመ አያቴ፣ ከሃለቃ ተወልደ መድኅን ገብሩ የተገኘ ታሪክ ነው።



ሁለተኛው ቃልም፣ "ዓላማ" በትግርኛም "ዒላማ" (Target) ወይም ምልክት ማለት ሲሆን፣ በጦርነት ጠላት የተደበቀባትን ጉራ ለመጠቆም የሚያገለግል ጠቃሽ ነው። እንግዲያውስ ሰንደቅ-ዓላማ የሚሉት ሁለቱ ቃላት፤ በረዥም ዕንጨት (በሰንደቅ) የተሰቀለ ምልክት ወይም ጠቃሽ (ዓላማ) ማለት ሲሆን፤ "ተመልከት ዓላማህን፣ ተከተል አለቃህን..." ሲል፣ ጦሩ አለቃውን ተከትሎ፣ ዓላማውን (ታርጌቱን) ተመልክቶ፣ ወደ ጠላት እንዲያነጣጥርና እንዲመታ፣ ጠላቱንም እንዲያጠቃ የሚነግር መሆኑን ለመረዳት ይቻላል። ከዚህም በማያያዝ አንድ በወቅቱ የተዘፈነ ዘፈን፦

"የጠቅልል አሽከር፣ ጀግናው ማማሩ፣
"ዓይኑ ተመልካች፣ ጠበንጃው ጡሩ፣
"ኣረማመዱ፣ ቁመናው ኩሩ፣
"ሩቅ ተመልክቶ፣ ማነጣጠሩ..."       የሚል ነበር።

ወደ ኣምስት መቶ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊትም፣ ቀዳማዊ ምኒልክ የጽላተ-ሙሴ ታቦትን ይዞ አክሱም ሲገባ፣ ኢትዮጵያም የሕገ ኦሪትን ስርዓት ስትቀበል፤ "ሃገራችን የእግዚአብሔር ብርሃን በራላት" ተብሎ ከአረንጓዴው በላይ የብጫ ቀለም "ብርሃን" እንደኣከሉበት አፈ-ታሪኩ ይነግረናል። ኣሁንም የሸማን ጨርቅ ወይባ በተባለው፣ ብጫ ቀለም ባለው ቅጠል ቀጥቅጠው በመንከር ነበር የሠሩት። (ዛሬም ቢሆን በወይባ ቅጠል ጭማቂ የተነከረ ልብሰ-መነኰሳት ብጫ ቀለም አለው።) እነዚህም ሁለት ቀለማት እስከ ኣብርሃ ወኣጽብሓ ዘመነ መንግሥት፤ ኢትዮጵያም የክርስትና ሃይማኖትን እስከ ተቀበለችበት ዘመን ድረስ የሃገራችን ሰንደቅ-ዓላማ ሆነው፣ ለብዙ ዘመናት ጸንተው ቆይተዋል።



በሦስት መቶ ሠላሳ ዓመተ-ምሕረት (ከክርስቶስ ልደት በኋላ) አባ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን ክርስትናን በኢትዮጵያ በሰበኩ ደግሞ፣ "ወንጌል የኦሪት ፍሬ ነው፣ በክርስቶስ መስቀልና ደምም የተገኘ ነው" በማለት፣ ከሁለቱ ቀለማት በላይ ቀይ ቀለም ጨምረው፣ ሰንደቅ-ዓላማውን ሦስት ኅብር፣ ማለትም አረንጓዴ፣ ብጫና፣ ቀይ ኣደረጉት።

ከአበው ቅድመ አያቶቻችን የሰማነውና የተማርነው የሰንደቅ ዓላማ ጥንታዊ አመጣጥ አፈ-ታሪክ ባጭሩ ይኸው ሲሆን፤ ታሪኩ ግን በዚህ

ኢያበቃም። በየዘመናቱ ሰንደቅ ዓላማችን በልዩ ልዩ ንጉሠ ነገሥትና መሪ፣ በመሳፍንትም ዘመን ምን ዓይነት ሁኔታዎች አሳልፉ ይሆን?



<u>ጥንታዊቷ የኢትዮጵያ ሰንደቅ-ዓላማ</u>።

ሰንደቅ-ዓላማችንም በዚሁ መልኳ ለብዙ ዘመናት ቆይታለች። ሰንደቅ-ዓላማ "ንጉሠ-ነገሥት ዘኢትዮጵያ"(6) ተብሎ የነገሥታት ሁሉ ንጉሥ በመሆን ከነገሠው ብቻ ስትገኝ፣ ሌሎች ከበታቹ ያሉት ተራ ንጉሦች ግን የየራሳቸውን ይዘው፣ የሸዋ፣ የጐጃም፣ የትግሬ፣ የወሎ... ንጉሥ ተብለው ይጠሩ ነበር እንጂ "ኢትዮጵያ" ኣይባሉም። ኢትዮጵያ የሚባለው በሊቀ-ጳጳሳት የሚቀባው ንጉሠ-ነገሥቱ ብቻ ነበር። ሌሎች ንጉሦችም የየራሳቸው የሆኑ ልዩ-ልዩ ሰንደቅ ዓላማዎችና የተለያዩ አርማውችም ሊኖሯቸው ይችላሉ። በየዘመናቱም ኣንዳንዱ ንጉሠ-ነገሥት አርማውን በሰንደቅ-ዓላማ ላይ ሲያትም፣ ሌላውም ይህ አልበቃ ሲለው፣ ኅብረ-ቀለማቱን የላዩን ወደ ታች፣ የታቹን ወደ ላይ ሲገለብጥ፣ የሚቀጥለውም ንጉሥ መልሶ ሲያቀናው፣ እንዲህ እያለ የፉክክር ቤት ሆኖ እስከዛሬ ድረስ ተቆይቷል።



ሃፄ ኃይለሥላሴ በነገሡ ጊዜ ስማቸውን ከላይ የጠቀስኩት ቅድመ አያቴ፣ ሃለቃ ተወልደ መድኅን ገብሩ፣ ከንጉሡ ዘንድ ቀርበው ነበርና፣ የሰንደቅ-ዓላማ ጥንታዊና ታሪካዊው አመጣጥ ለንጉሡ ኣስረድተው፤ "የቅጠል ልምላሜ ከስር፣ የኣበባና የብርሃን ቀለም ብጫው ቀጥሎ፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ ቀይ፣ የፍሬ ምልክት" መሆን ይገባል ብለው ሲገልጹላቸው፣ ንጉሡም በነገሩ ተስማሙበት። የኅብረ ቀለማቱ ስርዓትም እንዲታረም ቢሞክሩ፣ ቦሊቭያ (Bolivia) የተባለች የደቡብ

አሜሪካ አገር ቀድማ ይህንኑ የኅብረ-ቀለማት በተባበሩት መንግሥታት አስመዝግባለች ስለ ተባለ፣ "ማስተካከሉ ብዙ ችግር አለበት..." ተብሎ፣ ሰንደቅ ዓላማው ሳይታረም የታቹ ላይ፣ የላዩ ታች፣ ተዘቅዝቆ ቀረ።



ቦሊቪያ Bolivia

የዚህም ታሪክ እውነተኛነት በአዲስ አበባ የጽሕፈት ሚኒስተር መዝገብ ቤት (archives) ለተባበሩት መንግሥታት የተጻፈ ደብደቤ ካለ፣ መዝገብ ቤቱ መርምሮ ቢያጣራና፣ የታሪኩም ሓቀኛነት ማስረጃ ከተገኘ ለአንባብያን ቢያቀርብ፣ ለታሪኩ ተጨማሪ ክብደት ይሰጠዋል። ስለዚህ ጉዳዩን የመዝገብ ቤቱ ሓላፊዎች እንዲያተኩሩበት አደራ! እንላለን።

በዚያን ጊዜ የተባበሩት መንግሥታት ሕግና ስርዓት ይህንን ይከለክል ኖሮ እንደሆነ፤ ዛሬ ግን ከ1960 ዓ.ም. ወዲህ ነፃ ከወጡት አገሮች አንዷ፣ ጋና (Ghana) ይኸው እንደ ቦሊቪያ የመሰለ ሰንደቅ-ዓላማ አስመዝግባ ተገኛለች። ስለዚህ በዛሬ ጊዜ ትክክለኛው የኅብረ-ቀለማት ቅደም ተከተል ለማረም ቢፈለግ በተባበሩት መንግሥታት በኩል ችግር የሚኖር አይመስለንም።



ጋና Ghana

አንዳንድ ዘመናውያን ጸሓፊዎች ግን የሃገር ሽማግሎችና በሃገር ውስጥ የቆየውን ጥንታዊ አፈ-ታሪክ አጠያይቀው ሳይመረምሩ፣ በቅዱሳት መጻሕፍትም ያለውን የሰንደቅ ዓላማ ጥንታዊነት ማስረጃ ሳይገነዘቡ፣ "ኢትዮጵያ ባንዴራም አርማም አልነበራትም፣ ባንዴራ የዘመን አመጣሽ፣ እንዲያውም ከፖርቱጊዞችና ቱርኮች ወዲህ የመጣ ነው..." የሚሉ አይጠፉም። ጥንታዊትዋ ኢትዮጵያ ግን የሸማ ጨርቅ ቀለም ነክሮ በዘንግ ማንጠልጠል ይቅርና፣ ከአፈር ንጥር አንጥራ የወርቅ፣ የብርና፣ የነሓስ (Bronz) ብሮችና ሳንቲሞችም እንደነበሯት ታሪክ[7,8] ይመሰክራል። እንደ ዛሬው በየሕንፃውና በየአውራ ጐዳናው፣ በየዕለቱም ባንዴራ የማውለብለብ ልማድ አይኑር እንጂ፤ ሰንደቅ-ዓላማ የሚባል ፈጽሞ አልነበረም ማለት ትክክል አይመስለንም። ለምሳሌ

አርማ ይጠቀሙ እንደነበር የሚያሳይ በአክሱም ሓወልት ጫፉ ላይ፣ ከበስተጀርባው፣ ክብ የሆነ የጋሻ አርማ መሳይ ቅርጽ በግልጽ ይታያል።

የተለያየ አርማና ሰንደቅ-ዓላማ በየክፍለ ሃገራቱ መኖር በሌሎችም ሃገሮች የተለመደ ነው። ለምሳሌ በአሜሪካን አገር እያንዳንዱ ክፍለ ሃገር (State) ካሊፎርንያ፣ አሪዞና፣ ቴክሳስ... የየራሳቸው የሆነ ባንዴራና አርማ ብቻ ሳይሆን፣ የየራሳቸው የሆነ እንስሳ፣ ወፍ፣ ቢራቢሮ... ወዘተ. አሏቸው። በአንድነት "አሜሪካ" ሲባሉ ግን የ51 ከዋክብትና፣ የቀይና ነጭ ሰረዝ የሆነው ሰንደቅ ዓላማቸው የአንድነታቸው ምልክት ነው።

ለኛም እነዚህ አረንጓዴ፣ ብጫ፣ ቀይ፣ ኅብረ-ቀለማት ክርስትያን፣ እስላም ሳይባል፣ የመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሕብረትና ኣንድነት ምልክት ናቸው። በዓለምም ሁሉ የኢትዮጵያ ሰንደቅ-ዓላማ መሆናቸው ተጋንነው የታወቁት ጣልያን ኢትዮጵያን ደግማ በወረረችበት ዘመን ነው። አሁን በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በብዙ ኣህጉሮች፣ በተለይ በምዕራባዊው ዓለም በልብስ፣ በቆብ፣ በሌላም ቆሳቁስት ላይ እያተሙ በባንዴራችን ሲያጌጡ ይታያል። ብዙውን ጊዜ ይህ ጌጥ የጭቁኖች የተቃውሞ ምልክት መሆኑ ይታወቃል። ያን ጊዜ ኢትዮጵያ በሓያሉ የፋሺስት መዳፍ ስር ወድቃ ብትጠቃም፣ ተዋግታ ማሸነፏ፣ ነፃነቷንም ከአምስት ዓመታት የመራራ ትግል በኋላ መልሳ ማግኘቷ፣ ለዓለም ጭቁኖች ሁሉ ይኸ ታሪኳ ታላቅ ተስፋ ሆኗቸው፣ በትግላቸውም ሁሉ ጽናትና ብርታት ሰጪ ነው።

እነዚህ ሦስቱ ኅብረ-ቀለማት የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ምልክት ናቸው። ዛሬም በፌዴራላዊው ዘመን ያው በድሮ ጊዜ እያንዳንዱ ክፍለ ሃገር የየራሱ ባንዴራ እንደነበረው፣ ልዩ-ልዩ ሕዝቦች፣ ክፍለ-ሃገሮችና አህጉሮች የየራሳቸው የሆነ ሰንደቅ ዓላማና አርማ ቢኖራቸውም ቅሉ፣ ለጦርነት ሲወጡ ግን በዚህች ሰንደቅ ዓላማ ስር ተባብረው በመዝመት ለኣነድነታቸውና ትብብራቸው ምልክት የሆነች ይህች ሰንደቅ ዓላማ ናት። ከዚያም ታልፎ በዓለም ሃገራት ሁሉ በየኤምባሲውና በየሰልፉ ሸንጎ፣ በኦሌምፒክና በሌላም የስፖርት መድረኮች ስትታይ ይህች ሰንደቅ ዓላማ ለሁሉ ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ታሪካዊ ቅርስና የኩራት ምንጭ ሆና ለዘልዓለም ስትውለበለብ ትኖራለች።

ገ/ኢ. ጐርፉ።

# ጥቅሶች

1) ኦሪት ዘጸአት 17፡ 8-11
2) ኦሪት ዘሁልቅ 17፡ 1-10
3) ወንጌለ ማቴዎእ 21፡ 8-9
4) P. 105, Traditions De Tsazzega Et Hazzega, Johannes Colmodin. Rome 1902
5) መዝ-ዘዳ፡ 20፡ 5
6) ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፡ "ኣንተ ኢትዮጵያ፡ ኢትዮጵያ የምትለው፤ ኢትዮጵያ ካለ እኔ ምንም አይደለችም፤ ዕድሏ ከኔ ጋር የተሳሰረ ነው። እኔ ነኝ የማደርሳት፤ ካለ እኔ ትኖራለች ብለህ ኣታስብ።"
ብጅሮንድ ተክለ ሃዋርያት፡ "ለምን እንዲህ ያስባሉ? ኢትዮጵያኮ ሕያው ነች፤ እኛ ሁላችንም ሓላፊዎች ነን..." p. 170 Pioneers of Change in Ethiopia. Bahru Zewde
7) ጥንታውያን የአክሱም ነገሥታትና የአሠሯቸው ገንዘቦች፤ ኣዝማች ክንፉ ኪዳኔ፤ በ. በትሪንጋሊ (Ba Tringali) ማተምያ ቤት፤ አሥመራ 1960 ዓ.ም. (1967)
8) Aksum An African Civilization of Late Antiquity, Stuart Muroe-Hay 1991